## ምዕራፍ ፲፩

### ዘትስብእት ምንባብ

፩ በስመ እግዚአብሔር ሥሉስ በግጻዌ፡ዋሕድ በህላዌ፡ዘኢይረከብዎ በልባዌ ዘይእኅዝ ዓለመ ምድራዌ፡ለስብሐተ መንግሥቱ ዘረሰየ ዓለመ ሰማያዌ፡ሎቱ ንፌኑ ስብሐተ መርጡላዌ፡ ወቁርባነ ወንጌላዌ፡ ለዓለመ ዓለም አሜን፡፡

፪ ንጽሐፍ እንከ ዘለፉ ዕበዶሙ ለአንጢዲቆማርያጦስ እለ እሙንቱ ፀረ ማርያም እለ ይብሉ እምድኅረ ወለደቶ ለመድኃኒነ ተደመረት ምስለ ዮሴፍ፡፡ገብሩ ሎሙ ምክንያተ እምቃለ ወንጌላዊ ዘይቤ ኢያእመራ ዮሴፍ እስከ አመ ወለደት፡፡ወእሙንቱሰ ፈከርዎ ለዝ ቃል ኀበ ብሂለ ተደመረት እምድኅረ ወለደቶ ለመድኃኒነ፡፡ወብሂለ ኢያእመራሰ ይትረጎም ኀበ አእምሮ ወኀበ ኢየእምሮ ኀበ ሩካቤ ወኀበ ኢሩካቤ፡፡በእንተ አእምሮ ሩካቤሰ ትብል ቅድስት ኦሪት ወአእመራ አዳም ለሔዋን ብእሲቱ ወወለደት ሎቱ ቃየልሃ ወትቤ አጥረይኩ ብእሴ በእንተ እግዚአብሔር፡፡ ዘፍ፬፥፩ ማቴ፩፥፳፭

፫ ወካዕበመ ትብል ቅድስት ኦሪት ትብል ቅድስት ኦሪት ወአእመራ አዳም ለብእሲቱ ወወለደት ሎቱ ሴትሃ፡፡ዝሰ ይትረጎም ኀበ አእምሮ ሩካቤ ዘሙላደ ዘርእ፡፡ወበእንተ ኢያእምሮ ሩካቤኒ በእንተ ቅጥቃጤ ርስአን ይብል መጽሐፈ ነገሥት ዳዊትሰ ንጉሥ ልህቀ ወኀለፈ መዋዕሊሁ ይከድንዎ አልባሰ ወኢያመውቆ፡፡ወይቤሉ ደቂቁ ለዳዊት ይኅሥሡ ለእግዚእነ ለንጉሥ ወለተ ድንግለ ወያምጽእዋ ኀበ ንጉሥ ወትሰክብ ምስሌሁ ወትሕቅፎ ወታስተማውቆ ወይሙቅ እግዚእነ ንጉሥ፡፡ወኀሠሡ ወለተ ድንግለ ሠናይተ እምኵሉ ደወለ እስራኤል ወረከቡ አቢሳሃ ሰሜናዊተ ወወሰድዋ ኀበ ንጉሥ ወነበረት ትትለአኮ ወንጉሥሰ ኢያእመራ፡፡ዝኒ ይትረጎም ኀበ ኢያእምሮ ሩካቤ፡፡ወዘይቤሰ ወንጌላዊ ወኢያእመራ ዮሴፍ እስከ አመ ወለደት፡፡ይትረጎም ኀበ ኢያእምሮ ፅንሳ ለድንግል ዘነበረ እንዘ ይትሔዘባ ከመ እም ካልዕ ኮነ ወእመ አኮ

## ምዕራፍ ዐሥራ አንድ

### የትስብእት ምንባብ

፩ በአካል ሦስት በህልውና አንድ በሆነ በመመርመር ገንዘብ በማያደርጉት ምድራዊውን ዓለም ፈጥሮ በሚገዛ ለመንግሥቱ ምስጋና ሰማያዊን ዓለም በፈጠረ በእግዚአብሔር ስም የቤተመቅደስን ምስጋና የወንጌልንም ቁርባን ለርሱ እናቀርባለን ለዘላለሙ አሜን::

፪ የአንጢዲቆማርያጦስን የስንፍናቸውን ተግሣጽ ከእንግዲህ እንጽፋለን:: እኒሁም መድኒታችንን ከወለደች በኋላ ከዮሴፍ ጋር ተገናኝታለች የሚሉ ፀረ ማርያም ናቸው:: ከወንጌላዊ ቃል ዮሴፍ እስክትወልድ ድረስ አላወቃትም ያለውን ለራሳቸው ምክንያት አደረጉለት:: እነርሱስ ይህን ቃል መድኃኒታችንን ከወለደች በኋላ ተገናኛት በማለት ተረጎሙት፥ አላወቃትም ማለት ግን በማወቅና ባለማወቅ በመገናኘትና ባለመገናኘት ይተረጎማል:: ስለግንኙነት ማወቅ የከበረች ኦሪት አዳምም ሚስቱ ሔዋንን ዐወቃት ቃየልንም ወለደችለት ስለ እግዚአብሔርም ወንድ ልጅ አገኘን አለች ትላለች:: ዘፍ፬፥፩ ማቴ፩፥፳፭

፫ ዳግመኛም የከበረች ኦሪት ቃየል ሚስቱን ዐወቃት ሄኖስንም ወለደችለት ትላለች:: ዳግመኛም የከበረች ኦሪት አዳምም ሚስቱን ዐወቃት ሴትንም ወለደችለት ትላለች:: ይህም ዘር ለመተካት ግንኙነትን በማወቅ ይተረጎማል:: ግንኙነት ስለአለማወቅም ስለሽምግልና ድካም መጽሐፈ ነገሥት ንጉሥ ዳዊትም አረጀ ዘመኑም አለፈ ልብስ ያለብሱታል ነገር ግን አያሞቀውም ይላል::የዳዊት ልጆችም ለጌታችን ለንጉሥ ድንግል ልጅ ይፈልጉለት ወደ ንጉሥም ያምጧት ከእርሱ ጋር ትተኛለች አቅፋም ታሞቀዋለች፡ ጌታችን ንጉሥም ሙቀት ያገኛል አሉ:: ሰሜናዊት አቢሳን እስኪያገኙ ድረስ ከእስራኤል አውራጃዎች ሁሉ ያማረች ድንግል ሴት ልጅ ፈለጉ ወደ ንጉሥም ወሰዷት እያገለገለችውም ተቀመጠች፥ ንጉሥ ግን አያወቃትም ነበር:: ይህም ግንኙነትን በአለማወቅ ይተረጎማል:: ወንጌላዊም እስክ ትወልድ ድረስ ዮሴፍ አላወቃትም ያለው ግን ከሌላ እንደሆነ ወይም በጉረምሶች ልማድ በጉልማሶች ማሳት ፅንሳ እንደሆነ እየታዘባት የኖረውን የድንግል ፅንሷን ባለማወቅ ይተረጎማል:: ከዚያ አስቀድሞ

www.ethiopianorthodox.org

እምአስፍጠ ወራዙት ዘሕገ መሐዛን፡፡ እስመ
ኢሰምዐ እምቅድመዝ ፅንሰ ድንግልናዌ ወል
ደተ እንበለ ሩካቤ፡፡ወበእንተዝ ኢያእመራ
እስከ አመ ወለደት ከመ በድንግልና ፀንሰቶ
ለወልደ አብ፡፡

፬ ወሶበ ዜነወቶ ሰሎሜ ወለቱ ከመ
ተረክበ ማኅተመ ድንግልናሃ እምድኅረ ወለደ
ቶ ውእተ ጊዜ አእመረ ከመ በድንግልና ፀንሰ
ት፡፡ወሶበ ርእዮሙ ለሐራ ሰማይ እንዘ ይጼዐቁ
ውስተ በዐት ኀበ ተወልደ ወያስተበርኩ ውስተ
ጎል ኀበ ሰከበ ውእተ ጊዜ አእመራ ከመ እመ
እግዚአብሔር ይእቲ፡፡ወሶበ ርእዮሙ ለኖሎ
ት እንዘ ያቄርቡ ሎቱ መሐስአ እመራዕዩ
ሆሙ ውእተ ጊዜ አእመረ ከመ እግዚአ ሰብእ
ወእንሰሳ ውእቱ ዘተወልደ እምኔሃ፡፡ወሶበ ርእ
ዮሙ ለሰብአ ሰገል እንዘ ያቄርቡ ሎቱ ወርቀ
ከርቤ ወስኂነ ውእተ ጊዜ አእመረ ከመ እግ
ዚአ ነገሥት ወመንግሥት ውእቱ ዘተሠገወ
እምኔሃ፡፡ወሶበ ውዕየ አጻብዒሃ ለሰሎሜ አመ
ገሰሰት አንቀጸ ሥጋሃ ለድንግል ውእተ ጊዜ
አእመራ ከመ እመ እሳት ይእቲ፡፡ወካዕበመ
ሶበ ጥዕየ አጻብዒሃ ለሰሎሜ አመ ገሰሰቶ ለሕ
ፃን ውእተ ጊዜ አእመራ ለድንግል ከመ እመ
ሕይወት ወማኅየዊ ይእቲ፡፡ውእቱ ዝ ፍካሬ
ሁ ለብሂለ ኢያእመራ ዮሴፍ እስከ አመ
ወለደት ይተረጐም ኀበ ኢያእምሮ ፅንሳ ዘዘ
ከርና ቀዳሚ፡፡ ማቴ፩+፲፭ ሉቃ፪+፳-፳

፭ ወእምድኅረ ወለደትሰ አእመራ
ከመ ኃይል ዘኢያስተርኢ እንዘ ኢይትነሠት
ማኅተመ ድንግልናሃ፡፡እመሰ ይብሉ እምድ
ኅረ ወለደቶ ለመድኃኒነ ተደመረት ምስለ ዮሴ
ፍ ድሙራን ምስለ አጋንንት ርኩሳን ወኅቡ
ራን ምስለ ሠራዊተ ቤልሆር ጽልሙታን፡፡
ጥቀ ይኄይሰ ዕበደ ዚአሆሙ ለአይሁድ እም
እበደ እሉ እለ ይሰመዩ ፀረ ማርያም ዘውእቶ
ሙ አንጢዲቆማርያጦስ፡አይሁድሰ ይብሉ በኢለ
ብዎቶሙ አኮኑ ወልደ ዮሴፍ ውእቱ ዘለሊነ
ነአምር አባሁ ወእሞ፡፡እፎ እንከ ይብለነ እም
ሰማይ ወረድኩ እስመ መሰሎሙ በዘርአ ሙ
ላድ ዘተወልደ እማርያም ወኢያእመሩ ከመ
በብስራተ ገብርኤል ተሠገወ:: ወበእንተዝ ገብ
ሩ ሐሜተ ላዕለ ፅንሳ ድንግልናዊ እስመ ተመ
ሥጠረ እምኔሆሙ በመንጦላዕተ ጥበቢሁ ለእግዚ
አብሔር፡፡እስመ ኢያብሰራ መልአክ በቅድመ
ጉባኤ ወኢዜነዋ በቅድመ ነገደ ሕዝባ፡፡ወበእ
ንተዝ አምሰልዎ ለዕንቍ ዘውስተ ከርሣ ለንዋየ
በድንግልና ፅንስን ያለ ግንኙነት መውለድን
አልሰማምና፡፡ ስለዚህም እስከወለደችበት ጊዜ
ድረስ የአብን ልጅ በድንግልና እንደፀነሰችው
ዐላወቀም፡፡

፬ ልጁ ሰሎሜ ከወለደችው በኋላ
ማኅተመ ድንግልናዋ እንደተገኘ ስትነግረው ያን
ጊዜ በድንግልና እንደፀነሰች ዐወቀ፥ የሰማይ
ሠራዊት ወደ ተወለደበት ዋሻ ሲወጡና
ሲወርዱ በተኛበትም በረት ሲሰግዱ ቢያያቸው
ያን ጊዜ የአምላክ እናት እንደሆነች ዐወቀ፡፡
እረኞች ከመንጋቸው ጠቦት ሲያቀርቡለት
ቢያያቸው ያን ጊዜ ከእርሷ የተወለደው
የሰዎችና የእንስሳት ጌታ እንደሆነ ዐወቀ፡፡ ሰብአ
ሰገል ወርቅና ከርቤ ሽቱም ሲያቀርቡለት
ቢያያቸው ያን ጊዜ ከእርሷ ሰው የሆነው
የነገሥታትና የመንግሥታት ጌታ እንደሆነ
ዐወቀ፡፡ ሰሎሜ የድንግልን አፈ ማኅፀን በዳሰሰች
ጊዜ የሰሎሜ ጣቶቿ ቢቃጠሉ ያን ጊዜ የእሳት
እናቱ እንደሆነች ዐወቃት፡፡ ሁለተኛም ሰሎሜ
ሕፃኑን በዳሰሰችው ጊዜ ጣቶቿ ቢድኑ ያን ጊዜ
ድንግል የሕይወትና ሕይወትን የሚሰጥ የእርሱ
እናት እንደሆነች ዐወቃት፡፡ ዮሴፍም እስክ
ትወልድ ድረስ አላወቃትም የማለት ትርጉም
ይህ ነው፥ አስቀድመን እንደተናገርነው ፅንሷን
ባለማወቅ ይተረጐማል፡፡ ማቴ፩+፲፭ ሉቃ፪+፳-፳

፭ ከወለደች በኋላ ግን የማይታይ
ኃይል በማኅፀኗ እንደተፀነሰ ከእርሷም ማኅተመ
ድንግልና ሳይለወጥ በሚታይ ሥጋ እንደተወለደ
ዐወቀ ፡፡ መድኃኒታችንን ከወለ ደችው በኋላ
ከዮሴፍ ጋር ተገናኝታለች የሚሉት ግን
ከርኩሳን አጋንንት ጋር የተቆጠሩ ናቸው፥
ጨለማን ከለበሱ የቤልሆር ሠራዊት ጋር
ማኅበረተኞች ናቸው፡፡ ከእኒህ ፀረ ማርያም ከተ
ባሉ አንጢዲቆማርያጦስ ስንፍና የአይሁድ
ስንፍና እጅግ ይሻላል፥ አይሁድ ባለማስተ
ዋላቸው እኛ አባቱንና እናቱን የምናውቃቸው
የዮሴፍ ልጅ አይደለምን እንግዲህ እንዴት ከሰ
ማይ ወረድሁ ይለናል አሉ ከማርያም በመዋለጃ
ዘር የተወለደ መስሏቸዋልና፥ በገብርኤል የም
ሥራችም ሰው እንደሆነ ዐላወቁም ስለዚህም
በድንግልና ፅንሷ ላይ ሐሜት ተናገሩ የእግዚ
አብሔር የጥበባቱ መጋረጃ ከእነርሱ ተሠው
ሯልና፡፡ መልአኩም በጉባኤ ፊት አላበሰራትም
በወገኖቿ ፊት አልነገራትምና፡፡ ስለዚህም በማኅ
ፀኗ ያለውን ዕንቍ በወንድና በሴት መፈላለግ
ከሆነ የሥርቆት ገንዘብ ጋር አመሳሰሉት፡፡

ስርቅ ዘሥምረተ ብእሲ ወብእሲት፡፡ልማድ ውእቱ እምአዳም ወሔዋን እስከ ኅልቀተ ዓለም ወልደትሰ ዘእምባሕቲታ ብእሲት ኢኮነ እምቅድመዝ ወኢ ይከውን እምድኅረዝ፡፡እስመ በእግዚአብሔርናሁ ፈጠረ ለርእሱ ሐዲሰ ልደተ፡፡ ወበእንተዝ ኢያ እመርዎ ደቂቀ እስራኤል ለጥበበ እግዚአ ብሔር:: በከመ ይቤ ጳውሎስ ወፈቀዱ ይቁሙ በጽድቀ ርእሶሙ ወለጽድቀ እግዚአብሔርሰ ስእኑ ገኒየ፡፡እንዘ ይመስሎሙ ዘይቀንዑ ለሕገ ኦሪት ሰቀልዎ ለመጣዬ ኦሪት፡፡ወእንዘ ይቀ ንኡ ለሕገ ሙሴ ሰቀልዎ ለአምላከ ሙሴ፡፡ ወካዕበመ እንዘ ይቀንኡ ለአምልኮ እግዚአ ብሔር ሰቀልዎ ለወልደ እግዚአብሔር፡፡ ሉቃ ፩፥፴፭ ዮሐ፩፥፲፪ ሮሜ፲፥፱

፪ ወበእንተዝ ይቤ መድኃኒነ ሥረይ ሎሙ አባ እስመ ዘኢየአምሩ ይገብሩ፡፡ ወእ ሉሰ መናፍቃን እለ ንብሎሙ ፀረ ማርያም ይቤሉ እምድኅረ ወለደቶ ለመድኃኒነ ተደመ ረት ምስለ ዮሴፍ ፡፡አይ ልብ ኀለየ ዘመጠነዝ ጽር ፈተ ወአይ አፍ ደፈረ ከመ ይንብብ ዘንተ ጽርፈተ፡፡ዝ ነገረ ጽርፈት ይረኩስ እምእጽ ርቅተ ትክቶሆን ለአንስት ወእምደመ ሐሪሶን ዘሙላድ፡፡እስመ አንስት ይነጽሓ እምደመ ርኩሶን በሱባዔ መዋዕል ወእምደመ ሐሪሶን እመ ሮሰ ወለዳ በ፵ መዋዕል ወእመሂ ወለተ ወለዳ በ፹ መዋዕል፡፡ ዘሌ፲፪፥፩-፭

፫ ወእሉሰ እለ ጸረፉ ላዕለ ድንግል ናሃ ለወልዲተ መለኮት አልቦሙ ንጽሕ ኢበዝ ዓለም ወኢበዘይመጽእ ዓለም፡፡ወአልቦሙ ድ ምሳሴ ለኃጣውኢሆሙ ኢበንስሓ ወኢበጾዊም ፡፡ኢበጸልዮ ወኢበቀዊም፡፡ወእመኒቦ ዘተመ ይጠ እምሃይማኖቶሙ ውስተ ሃይማኖትነ ይደ ሉ ከመ ያጥምቅዎ ዳግመ እስመ ኢኮነ ጥም ቀቶሙ ከመ ጥምቀተ ክርስቶስ፡፡እስመ ነበቡ ጽርፈተ ላዕለ ስመ ክርስቶስ ወኢይጼልል ዲበ ምሥዋዮሙ ኃይለ ልዑል ወኢይበጽሖሙ ጽላ ሎተ መንፈስቅዱስ ለዘአርኰሱ ዜናሃ ለዘቀደ ሳ መንፈስቅዱስ፡፡

፬ እፎኬ ይብልዋ እምድኅረ ወለደቶ ለመድኃኒነ ተደመረት ዘኢያብሖ መንፈስቅዱ ስ ምስለ ዮሴፍ ለቀሪቦታ እምአመ አዕቀብዋ ሊቃነ ካህናት እስከ አመ ፀንሰቶ ለወልደ እግዚአብሔር፡፡እፎኬ ያበውሖ ለቀሪቦታ እም ድኅረ ወለደቶ፡፡አይ ዘሥጋ ይክል ቀሪቦታ ለጽርሐ መለኮት፡፡ አይ ብእሲ ይክል በዊኦታ ለማኅፈደ መለኮት፡፡ ኢሳይያስኒ ይቤ ወወሀ ብዎ ለብእሲ መጽሐፈ ዘኢየአምር መጽሐፈ

ከአዳምና ከሔዋን ጀምሮ እስከ ዓለም መጨረሻ ድረስ የተለመደ ነው፥ ብቻዋን ከሆነች ሴት መወለድ ከዚህ በፊት አልሆነም ከዚህም በኋላ አይሆንም በአምላክነቱ ለራሱ አዲስ ልደትን ፈጥሯልና:: ስለዚህም የእስራኤል ልጆች የእግዚአብሔርን ጥበብ ዐላወቁትም ጳውሎስ በገዛ ጽድቃቸው ይቆሙ ዘንድ ወደዱ ለእግዚ አብሔር ጽድቅ ግን መገዛት ተስኗቸዋል ለኦሪት ሕግ የቀኑ መስሎአቸው የኦሪትን አስገኚ ሰቀሉት፡ ለሙሴ ሕግ ቀንተው የሙሴን አምላክ ሰቀሉት ዳግመኛም ለእግዚአብሔር አምልኮ ቀንተው የእግዚአብሔርን ልጅ ሰቀሉት እንዳለ፡፡ ሉቃ ፩፥፴፭ ዮሐ፩፥፲፪ ሮሜ፲፥፱

፪ ስለዚህም መድኃኒታችን አባት ሆይ የማያወቁትን ያደርጋሉና ይቅር በላቸው አለ፡፡ እነዚህ ፀረማርያም የምንላቸው መናፍቃን ግን መድኃኒታችንን ከወለደችው በኋላ ከዮሴፍ ጋር ተገናኘች ይላሉ፣ ምን ዓይነት ልብ ይህን ያህል ድፍረት አሰበ፣ምን ዓይነት አንደበት ይህን ስድብ ይናገር ዘንድ ደፈረ፡፡ ይህ የስድብ ቃል ከሴቶች የመርገም ጨርቅ ከመውለድ አራስነት ደምም ይልቅ ይረክሳል፡፡ ሴቶች በሰባት ቀን ከርኩሰታቸው ደም ይነጻሉ ከአራስነታቸውም ደም ወንድ ቢወልዱ በአርባ ቀን ሴት ልጅም ቢወልዱ በሰማንያ ቀን ይነጻሉ፡፡ ዘሌ፲፪፥፩-፭

፫ እኒህ የአምላክን እናትን ድንግልና የሚሳደቡ ግን በዚህ ዓለም በሚመጣውም ዓለም አይነጹም፡፡ ለኃጢአታቸውም በመጸጸትም ቢሆን በመጾምና በመጸለይም ቢሆን በመቆምም ሥር የት የላቸውም፡፡ ከሃይማኖታቸው ወጥቶ ወደ ሃይማኖታችን የተመለሰ እንኳ ቢኖር ያጠምቁት ዘንድ ይገባል ጥምቀታቸው እንደ ክርስቶስ ጥምቀት አይደለምና፣ በክርስቶስ እናት ላይ ስድብን ተናግረዋልና በመሠዊያቸው የልዑል ኃይል አይጋርድም የልዑል ኃይል የጋረዳትን ስለድንግልናዋ ክህደትን ተናግ ረዋልና፡፡ መንፈስቅዱስ ያከበራትን የእርሷን ዜና ለሚያረካክሱት የመንፈስቅዱስ ጥላ አይደር ሳቸውም፡፡

፬ መድኃኒታችንን ከወለደችው በኋላ የካህናት አለቆች አደራ ካስጠበቁት ጊዜ ጀምሮ የእግዚአብሔርን ልጅ እስከትፀንሰው ድረስ ወደ ርሷ እንዳይቀርብ መንፈስቅዱስ ያላሰናበተውን እንደምን መድኃኒታችንን ከወለደችው በኋላ ከዮሴፍ ጋር ተገናኘች ይሏታል፡፡ ከወለደችው በኋላ እንደምን ይቀርባት ዘንድ ያሰናብተዋ ል፡፡የመለኮትን አዳራሽ ሊቀርባት የሚችል የት ኛው ሥጋዊ ነው፡፡ምን ሰው ወደ መለኮት አዳራሽ ሊገባ ይችላል፡፡ኢሳይያስም መጽሐፍ

፡፡ወይብል ኢይከል አንብቦታ፡፡ ዝ ውእቱ
ማኅተመ ድንግልናሃ ወዜና ንጽሐ ሥጋሃ በኢ
ቀሪበ ብእሲ፡፡ ኢሳ፷፱፥፲፪

፱ ሕዝቅኤልኒ ይቤ ርኢኩ ኆኅተ በም
ሥራቅ ኅቱም በዐቢይ መንክር ማኅተም፡፡
አልቦ ዘቦአ ዘእንበለ እግዚእ ኃያላን ቦአ ውስ
ቴታ ወወፅአ፡፡ዝኒ ዜና ማኅተም ዘአንቀጸ ሥ
ጋሃ፡፡ ሰሎሞንኒ ይቤ ገነት ዕፁት ዐዘቅት ኅት
ምት ፍናወ ዚአኪ፡፡ምንት ይትረከብ በኀበ ገነ
ት፡፡አኮኑ ፍሬ አስካል ጥዑም፡፡ወምንትኑ
ፍሬ አስካል ጥዑም፡፡ አኮኑ ኢየሱስ ክርስቶስ
ፍሬ ድንግልናሃ ለእሙ፡፡ወብሂለ ገነትሰ ዕፁ
ት ይትረጐም በአንቀጸ ሥጋሃ ዘዕፁት በመና
ስግተ ድንግልና፡፡ምንትኑ ካዕበ ይትረከብ ኀበ
ዓዘቅት ዘእንበለ ማይ ጥዑም፡፡ወምንትኑ ማይ
ጥዑም ዘእንበለ ኢየሱስ ክርስቶስ ዘይቤ በወን
ጌል ዘጸምአ ይምጻእ ኀቤየ ወይሰተይ፡፡ወብ
ሂለ ዓዘቅትሂ ኅትምት ኃይለ ድንግልናሃ ዘን
ጽሕት እም፡፡እስመ ኲሎሙ ነቢያት ሰመይዋ
ኅትምተ በድንግልሃ ወዕፁተ በእንተ አንቀጸ
ሥጋሃ፡፡ ሕዝ፵፯፥፩-፪ መኃ፬፥፲፪

፲ ስብሐት ለእግዚአብሔር ለዘቀደሳ
ወአንጽሓ ለዓለመ ዓለም አሜን፡፡

፲፩ ተፈጸመ ዘለፋሆሙ ለአንጢዲቆ
ማርያጦስ ዘውእቶሙ ፀረ ማርያም መም
ህራነ ርኩስ፡እለ ኢበጽሖሙ ጽላሎተ መንፈስ
ቅዱስ፡በከመ አርኰስዋ በቃለ አፉሆሙ
ለእመ ክርስቶስ፡ንሰምዮሙ ርኩሳነ እምነ ኲሉ
ዘነፍ ስ፡ ውስተ ገጸ ምድር ዘይትሐወስ፡
ወጽዩአነ እምገደላ አእዱግ ወአፍራስ፡ይቤ
ጊዮርጊስ ማኅሌታይ ለስመ ሥሉስ፡ ወዘፋኒ
ለቤተመቅደስ፡ ረድአ ትምህርቶሙ ለሐዋር
ያት ለጴጥሮስ ወጳውሎስ ወዘበምግባሩ እቡስ፡
ሰአሉ ሎቱ ሥርየተ ኃጣውእ አባግዓ ምሥ
ጢሩ ለኢየሱስ፡ ከመ ያርፍቆ እግዚአብሔር
ውስተ ሕፅነ አበ ዊሁ ሐዋርያት በቤተ መርዓ
ሐዳስ፡ ለዓለመ ዓለም አሜን፡ ወአሜን፡፡

……… /// ………

ለማያውቀው ሰው መጽሐፍ ሰጡት እርሱም
ላነባት አይቻለኝም አለ ይላል፡፡ የድንግልናዋ
ማኅተም ይህ ነው ወደ ወንድ ባለመቅረብም
የሥጋዋ የንጽሕና ዜና ይህ ነው፡፡ ኢሳ፷፱፥፲፪

፱ ሕዝቅኤልም ድንቅ በሆነ ታላቅ
ማኅተም የታተመች ደጃፍ በምሥራቅ አየሁ፥
ከኃያላን ጌታ በቀር የገባባት የለም፥ እርሱ
ገባባት ወጣም እንጂ አለ፡፡ ይህም የአፈ ማኅፀኗ
ማኅተም ዜና ነው፡፡ ሰሎሞንም የተዘጋች ገነት
የታተመች ጉድጓድ ጉዳናዎችሽ ናቸው አለ፡፡
በገነት ምን ይገኛል ጣፋጭ ፍሬ አይደለምን፥
ጣፋጭ ፍሬስ ምንድር ነው የእናቱ የድንግልናዋ
ፍሬ ኢየሱስ ክርስቶስ አይደለምን፡፡ የተዘጋች
ገነት ማለትም በድንግልና ቁልፍ በተዘጋች
አፈ ማኅፀኗ ይተረጐማል፡፡ ሁለተኛም ከጣፋጭ
ውኃ በቀር ከውኃ ጉድጓድ ምን ይገኛል፡፡ በወን
ጌል የተጠማ ወደኔ ይምጣ ይጠጣም ብሎ ከተና
ገረ ከኢየሱስ ክርስቶስ በቀር ጣፋጭ ውኃ ማን
ነው፡፡የታተመች የውኃ ጉድጓድ ማለት የንጽህት
እናቱ የድንግልናዋ ኃይል ነው፡፡ ነቢያት ሁላቸ
ው በድንግልናዋ የታተመች ስለ አፈ ማኅፀኗም
የተዘጋች ብለዋታልና፡፡ ሕዝ፵፯፥፩-፪ መኃ፬፥፲፪

፲ ላከበራትና በንጽህና ለጠበቃት ለእግዚአ
ብሔር ምስጋና ይሁን ለዘላለሙ አሜን፡፡

፲፩ ፀረ ማርያም የሆኑ የርኩሰት
መምህራን የአንጢዲቆማርያጦስ ተግሣጽ ተፈ
ጸመ፡፡ የመንፈስቅዱስ ጥላ ያላረፈባቸው እነርሱ
የክርስቶስን እናት በአንደበታቸው እንዳረከሷት
በምድር ላይ ከሚንቀሳቀሱ ነፍስ ካላቸው ሁሉ
ይልቅ የረከሱ ናቸው እንላቸዋለን፥ ከአህዮችና
ከፈረሶችም በድን ይልቅ የሸተቱ ናቸው፡፡
ለሥላሴ ስም የሚዘምር ለቤተ መቅደስም
የሚዘምር የሐዋርያት የጴጥሮስና የጳውሎስ
የትምህርታቸው ደቀ መዝሙር በሥራው ግን
በደለኛ የሆነ ጊዮርጊስ ተናገረው፡፡ የኢየሱስ
የምሥጢሩ መንጋዎች እግዚአብሔር በአዲሲቷ
ሠርግ ቤት በአባቶቹ በሐዋርያት እቅፍ እንዲያ
ስቀምጠው ለምኑለት ለዘላለሙ አሜን፡፡

……… /// ………